# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 346 ታህሳስ 17 2007

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዓርብ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. በባህርዳር ከተማ በርካታ ወገኖቻችን ሕይወታቸውን ያጡ በመሆናቸው የተሰማውን ጥልቅ ሀዘንና ቁጭትእየገለፀ ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ይመኛል። እንደዚሁም በዚሁ ዕለት በህወሓትና ብአዴን ሠራዊቶች ጥይት ለቆሰላችሁና ለተደበደባችሁ ወገኖቻችን ሁሉ ህመማችሁ ህመማችን፤ በእናንንተ ላይ የደረሰው በደል በሁላችንም ላይ የደረሰ መሆኑን እንድትረዱልን እንፈልጋለን።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአየር ኃይል አብራሪዎች ከነ ሂሊኮፕተራቸዉ ወያኔን ከድተዉ ተሰወሩ

ሚኒስቴሩ በሰጠው መግለጫ ተዋጊ ሔሊኮፕተሩ ባለፈው አርብ ክጧቱ 2 ሰአት ጀምሮ በመደበኛ የስልጠና ለምምድ ላይ የነበረ ሲሆን ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሄሊኮፕተሩ ከግንኙነት ውጪ በመሆኑ በሰራዊቱ በአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሁም በአጋሮች ለተከታታይ ቀናት እና ሰአታት ፍለጋ ሲደረግለት መቆየቱን አስታውሶ ሆኖም ተዋጊ ሄሊኮፕተሩ በከሐዲው ዋና አብራሪ አማካኝነት ቴክኒሻኑን እና ረዳት አብራሪውን በማስገደድ ኤርትራ ማረፉን የተገኙ መረጃአዎች ያሳያሉ ሲል ቅጥፈት የማይሰለቸው የፋሺስቱ አገዛዝ መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ይሁንና ባለፈው አርብ ያብራት የነበረውን ተዋጊ ሄሊኮፕተር ከረዳት አብራሪውና ከቴክኒሻኑ ጋር ይዞ ከፋሺስታዊው የወያኔ አገዛዝ የተሰወረው ሻምበል ሳሙኤል ግደይ የሚግ 23 ተዋጊ አውሮፕላን አብራሪ የነበረና በ1995 ኣ.ም ከከፍትኛ ትምህርት ተቋም አየር ሃይሉን የተቀላቀለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።ሻምበል ሳሙኤል ግደይ ከምርጫ 97 በሁዋላ አገዛዙ በሕዝቡ ላይ በሚያደርሰው በደል እና ጭፍጨፋ በአገዛዙ ላይ ጥያቄ ማንሳት መጀመሩንና በተለያዩ መንገዶች ተቃውሞ ማሰማት መቀጠሉ በወያኔዎቹ አለቆቹ ጥርስ ውስጥ ገብቶ እንዲቆይ ማድረጉን ከአየር ሐይል ምንጫችን ለመረዳት ችለናል።

የወያኔው መከላከያ ሚኒስቴር ተብዬ ባወጣው መግለጫዋና አብራሪው ሻምበል ሳሙኤል ግደይ ረዳት አብራሪውንና ቴክኒሻኑን አስገድዶ ኤርትራ አርፏል የሚለው መግለጫው የትግራይ ተወላጅ የሆነው ሻምበል ሳሙኤል ግደይ በስርአቱ ኢፍትሃዊነት ሲማረር እንደነበረ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው።

ከአኢትዮጲያ አየር ሃይል ጠፋ ከተባለው ተዋጊ ሄሊኮፕተር ውስጥ አብራሪውን ጨምሮ 3 የአየር ሃይል አባላት የነበሩ ሲሆን የኦሮሞ ተወላጅ ከሆነው ረዳት አብራሪ መቶአለቃ ቢልልኝ ደሳለኝ በስተቀር ዋና አብራሪው ሻምበል ሳሙኤል እና ቴክኒሻኑ ጲጋብርሀን ግደይ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ለፋሺስታዊው አገዛዝ ከፍተኛ የራስምታት መሆኑ ታውቋል።

ፋሺስቱ ወያኔ በትግራይ ወጣቶች የህይወት መስዋእትነት ለስልጣን ከበቃ በኋላ በሕዝባችን እና በሀገራችን ላይ ላለፉት 24 አመታት ለፈጸማቸው ግፍና ሰቆቃ በጅምላ የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ እና ትብብር ያለው ለማስመሰል ሲጥር መቆየቱ ይታወቃል። ሆኖም ይህንን አስከፊ ፋሺስታዊ አገዛዝ በመቃወም በ 10ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች በትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዴምሂት ስር በመሰባሰብ አገዛዙን ለማስወገድ ብረት .. ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ባህር ዳር ውስጥ አንድ እንግሊዛዊ ተገደለ

አንድ ለግዜዉ ማንነቱ በውል ያልታወቀ እንግሊዛዊ ባህር ዳር ዉስጥ ጊዮርጊስ እየተባለ በሚጣራዉ አካባቢ ሲንቀሳቀስ በአንድ የወያኔ የሚሊሺያ አባል በጥይት ተመትቶ መገደሉን ባህር ዳር ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። እንግሊዛዊዉን የገደለዉ ሚሊሺያ መሳሪያ ይዞ ድብ አንበሳ እየተባለ በሚጠራው ሆቴል አካባቢ ሚቹን ሲጠባበቅ እንደነበር ዘጋቢያችን ያነጋገረቻቸው ሰዎች ገልጸዋል። በሆቴሉ አካባቢ ጫማ በመጥረግ የሚተዳደሩ የአካባቢዉ ነዋሪዎች ገዳዩ መሳሪያውን ይዞ ከእነሱ ጋር ሲቀመጥና ሲንቀሳቀስ እንደነበር ገልጸው፣ በሰውየው ሁኔታ ግራ በመጋባት ከአካባቢው እንዲርቅ እንዳደረጉትና ራቅ ብሎ ሚችን ይጠባባቅ እንደነበር ተናግረዋል። ድርጊቱ ሲፈጸም ፖሊሶች በአካባቢው የነበሩ ሲሆን፣ ገዳይ ፈረንጁን ከገደለው በኋላ የላምንም ማንገራገር እጁን ለፖሊሶች መስረጠል። በጉዳዩ ዙሪያ የእንግሊዝ ኢምባሲንና የክልሉን ፖሊስ ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካምቱ ታዉቋል።

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ሃይለማርያም ደሳለኝ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን አስጠነቀቀ

የኢትዮጵያ ፓርላማ አሸባሪ ብሎ ከፈረጃቸው ድርጅቶች ጋር በቀጥታ እየተገናኙ የሀገራችንን ጥቅምና ሰላም ለማወክ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አሉ ሲል የወያኔዉ ተላላኪ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ተናገረ:: ኃይለማርያም ደሳለኝ በጠ/ሚኒስትሩ በጽ/ቤት በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ የፓለቲካ ፓርቲ አባላት እየታሰሩ መሆናቸውን አስመልክቶ በቀረበለት ጥያቄ በሰጠዉ ምላሽ አሸባሪ ከሚባሉ ቡድኖች በቀጥታ እየተገናኙና እያቀዱ ሀገር ለማሸበር እየዶለቱ የሚውሉ ሃይሎች መኖራቸውን በመጥቀስ መንግስት ይህንን እያየ ዝም አይልም ብሏል።

ሀገራችን እንደአንዳንድ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት እዚህም እዚያም ቦምብ የሚፈነዳባት ሀገር እንድትሆን አንፈልግም ያለዉ ኃይለማርያም ደሳለኝ መንግስት በሕጋዊነት በተመሰረቱ ፓርቲዎች ውስጥ ከሽብር ቡድኖች ጋር የሚተባበሩ ግለሰቦች ወይም መሪዎች ስላሉ የፓርቲው አባላት መሪዎቻችን ለምን ታሰሩ ብለው ሊጠይቁ አይገባም በማለት ተናግሯል። አመራሮቹ የታሰሩት ከሽብር ቡድኖቹ ጋር የተነጋገሩትን በድርጊት ለመፈጸም ሲንቀሳቀሱ መሆኑን ጠቅሶ መንግስት ሕግና ስርዓትን ማስከበሩ ተገቢ ነዉ ብሏል። ተቃዋሚዎች መንግስትን አጣብቂኝ ውስጥ ለመክተት የልማት ሥራዎች በሚከናወኑበት ቦታዎች ሰልፍ አካሂዳለሁ በማለት መንግስትን ይፈታተናሉ ያለዉ ኃይለማርያም ደሳለኝ እንዲህ አይነቱ አካሄድ በፍጹም አያዋጣም ብሏል።

... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ በባህር ዳር የወሰደዉ ፋሺስታዊ እርምጃ የብአዴንን ካድሬዎች ለሁለት መከፈሉ ተሰማ

ባሳለፍነው አርብ ታኅሣሥ 10 ቀን 2007 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ ድንገት የተቀሰቀሰውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በነዋሪዎች ላይ የወሰደው እጅግ አረመኔያዊ የሆነ የሐይል እርምጃ በብአዴን ካድሬዎች መካከል ቅራኔ መፍጠሩን የውስጥ ምንጮቻችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል። በተለይ በባህር ዳር አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የብአዴን ካድሬዎች አገዛዙ በባህር ዳር በንጹሃን ዜጎች ላይ የወሰደው የግድያ፤ የድብደባና የጅምላ እስር እርምጃ ከፍተኛ ቁጣ ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ መናገራቸው ታውቋል።

ከህዝባዊ ተቃውሞው ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የገቡት የጉጅሌው ወያኔ ቱባ ሹማምንት በጠሩትና ካሳለፍነው ቅድሜ ጀምሮ እየተደረገ ያለው ዝግ ስብሰባ በተቃውሞና በልዩነት እየተናጠ መቀጠሉን ያደረሱን ምንጮቻችን ካድሬዎቹ ፈጽሞ ሕዝብን ማሳመን የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ሲሉ መናገራቸውም ተመልክቷል። ንጹሃን ዜጎችን በአደባባይ በጥይት ደብድቦ መግደል፤ መደብደብና ማሰር የፖለቲካ ትርፉ ምንድነው ሲሉ ጉጅሌዎቹን የጠየቁት ካድሬዎቹ በባህር ዳር የተደረገው አረመኔያዊ እርምጃ በመጭው ምርጫ ላይ ከባድ ተጽእኖ ያጠላበታል ሲሉ ስጋታቸውን መሰንዘራቸው ታውቋል። ማንኛውንም ህዝባዊ ጥያቄ በሃይል እየደፈጠጠ 24 አመታትን በአንባገነንነት የተጓዘው እብሪተኛው ወያኔ ከመጭው ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊደርስበት የሚችለውን ሽንፈት ተከትሎ እንደ ከዚ ቀደም ሁሉ አሁንም በህዝብ ላይ ላለመተኮሱ ማረጋገጫችን ምንድነው ሲሉ የጠየቁ ካድሬዎችም መኖራቸውን ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በባህር ዳር ከተማ እየተደረገ ባለው ዝግ ስብሰባ ላይ በአንዳንድ የብአዴን ካድሬዎች እየተሰነዘሩ የሚገኙት ጥያቄዎችና ካድሬዎቹ እያሳዮት ያሉት የህዝብ ወገንተኝነት በቱባ ጉጅሌዎች ዘንድ ካለ መወደዱም በላይ ከፍተኛ መደናገጥን ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ ታውቋል። ምናልባትም ከዚህ ስብሰባ መጠናቀቅ በኋላ በካድሬዎቹ ላይ ቂም የቋጠሩት ነፍሰ ገዳዮቹ የወያኔ ቱባ ሹማምንት በተወሰኑ ግለሰቦች ላይ እርምጃ ሊያስወስዱ እንደሚችሉም ስጋት መኖሩን ምንጮቻችን አመልክተዋል። በተያያዘ ዜና በባህር ዳር ከተማ ዳግም የተቃውሞ እንቅስቃሴ በአንዳንድ ቀበሌዎች ላይ መኖሩ እየተነገረ ሲሆን እብሪተኛው አገዛዝ ከከተማዋ ነዋሪ በላይ የሚሆን የፌደራል ፖሊስ በሁሉም ቀበሌዎች አሰራጭቶ ህዝቡን በማስፈራራትና በማፈን ስራ ላይ መጠመዱም ታውቋል።

## ከታህሳስ 10 ቀን 2007 የአዲስ አበባና ባህርዳር አመጾች ምን እንማራለን?

ዓርብ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. አዲስ አበባ እና ባህርዳር በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን አስተናግደዋል። በአዲስ አበባ ሙስሊም ወገኖቻችን ከህወሓት ሰላዮች እይታ ውጭ በተደራጀ መንገድ በኑር መስኪድ ያደረጉት ተቃውሞ ቢያንስ ሶስት ቁም ነገሮችን አስገንዝቧል። እነዚህ ሶስት ነገሮች፣ (1ኛ) ምላሽ እስካላገኘ ድረስ የመብት ማስከበር ትግል በአፈና ተዳፍኖ እንደማይጠፋ፣ (2ኛ) ጽናት ካለ የወያኔ አፈናን የሚቋቋም ድርጅትና ተግባቦት መፍጠር እንደሚቻል፣ እና (3ኛ) ሙስሊሙን በተመለከተ የህወሓት አንድ-ለአምስት አደረጃጀት መፍረሱ ናቸው። ይህ ድል የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያንም የሚጋሩት የጋራ ድል ነው። በተለይም የወያኔ አንድ-ለአምስት አደረጃጀት የሚናድ መሆኑ በተግባር ማሳየታቸው እና የህወሓት ሰላዮች ሳይሰሙ ተቃውሞዓቸውን አደራጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸው የሚደነቅ ነው።

በዚሁ ዕለት በባህርዳር የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ከሕዝብ ጋር ሳይመክር በልማት ስም ያሻውን የሚያደርገውን እብሪተኛን ለመቃወም በአጭር ጊዜና በፍጥነት ተሰባስበው ቁጣቸው ማሰማት ችለዋል። በባህር ዳር ሕዝብ ልብ ውስጥ ለዓመታት ሲብሰለሰል የቆየውን የበደል ስሜት በዚህ አጋጣሚ ገንፍሎ ወጥቷል። በተለይም የወያኔ “ምርጥ ባርያ” መሆኑ የሚስፈነጥዘው ብአዴን በአማራ ሕዝብ ምን ያህል የተጠላና የተናቀ መሆኑ እንዲያውቅ ተደርጓል። ሆኖም ግን፣ ማናቸውንም ዓይነት ተቃውሞ የማያስተናዱት ህወሓትና ባርያው ብአዴን በባዶ እጁ ለተቃውሞ በወጣው ሕዝብ ላይ የጥይት ናዳ እንዲያወርድ ሠራዊታቸውን በማዘዛቸው እና ይህን ዘግኛኝ ትዕዛዝ የሚያስፈጽም ሠራዊት ያለ በመሆኑ ብዙ አዛውንት፣ ጎልማሶችና ወጣቶችን ለሞትና ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። የህወሓትና የብአዴን ሠራዊት ከዱላና ከገዳይ ጥይት ሌላ አንዳችም የአድማ መበተን እውቀት የሌለው መሆኑን የሚያሳዝን ነው፤ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ እንዲተኩስ ሲታዘዝ የሚተኩስ መሆኑም የሚያሳፍር ነው። በባህርዳር ከተፈፀመውም የኢትዮጵያ ሕዝብ (1ኛ) ሕዝባዊ አብዮት እንዲህ በደንብ ሳይታሰብበትም ሊቀሰቀስ የሚችል መሆኑ፣ (2ኛ) ህወሓት ሕዝብ አምርሮ ሲነሳበበት የሚደነግጥና የሚርበተበት ፈሪ መሆኑ፣ እና (3ኛ) በፈሪነቱ ምክንያትም በባዶ እጃቸው በወጡ አዛውንትና ህፃናት ጭምር የተኩስ እሩምታ ከመክፈት የማይመለስ መሆኑን አስተውሏል ብለን እናምናለን።

ህወሓትንና አገልጋዮቹን ከስልጣን ለማባረር በአዲስ አበባ እና ባህርዳር የተደረጉትን ማቀናጀት ግዴታ ነው። በሌላ አነጋገር የባህር ዳሩ ሕዝባዊ አመጽ አዲስ አበባ ኑር መስጊድ በታየው ዓይነት ብልሃት፣ ድርጅት እና ዲሲፕሊን ተመርቶ ቢሆን ኖሮ በባህር ዳር የተጫረው የነፃነት እሳት በመላው አገሪቷ ተቀጣጥሎ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ከታህሳስ 10 ከነበረው ፈጽሞ የተለየ በሆነ ነበር። ለወደፊቱም ማድረግ የሚኖርብን ይህ ነው። ሙስሊምና ክርስቲያኑ ተደጋግፎ አንዱ ዘንድ የጎደለው በሌላው አካክሶ የሁላችንም ጠላት የሆነውን ህወሓትን ከነ አገልጋዮቹ ከሥልጣን ማስወገድ የሁላችንም የጋራ ግዴታ ነው። ጠመንጃው የፍርሃቱ መሸሸጊያ ያደረገው ህወሓትም ጠመንጃውን የሚያስጥል መላ እና ዱላ መዘጋጀት ይኖርበታል። ህወሓትንና አጫፋሪዎቹን ከሥልጣን ለማባረር በጠንካራ ድርጅት፣ ዲሲፕሊንና ብልሃት የሚመራ ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ሕዝባዊ አመጽ ቅንጅት ሊኖር እንደሚገባ የታህሳስ 10 ቀን 2007 ትልቁ ትምህርት ነው። በዚህ ዕለት የህወሓትን ወደ ጠመንጃ የመሮጥ ወራዳ ባህርይን የሚያስቆም ኃይል የማደራጀት አስፈላጊነትም ጉልህ ሆኖ ወጥቷል። ዓርብ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓም አዲስ አበባና ባህርዳር የተፈፀሙትን አገናኝቶ ያነበበ ማንኛውም ሰው የሁለገብ ትግል ስልት ምንነትና አዋጭነት በገሃድ ይረዳል፤ ወደዚያ እያመራን መሆኑንም ይገነዛባል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዓርብ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. በባህርዳር ከተማ በርካታ ወገኖቻችን ሕይወታቸውን ያጡ በመሆናቸው የተሰማውን ጥልቅ ሀዘንና ቁጭትእየገለፀ ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ይመኛል። እንደዚሁም በዚሁ ዕለት በህወሓትና ብአዴን ሠራዊቶች ጥይት ለቆሰላችሁና ለተደበደባችሁ ወገኖቻችን ሁሉ ህመማችሁ ህመማችን፤ በእናንንተ ላይ የደረሰው በደል በሁላችንም ላይ የደረሰ መሆኑን እንድትረዱልን እንፈልጋለን። እንዲህ ዓይነቱ በደል እንዲያበቃ ደግሞ ህወሓት፣ ብአዴን እና በየክልሉ ያሉት አጋፋሪዎቹ ከሥልጣን መወገድ እንዳለባቸው ያለጥርጥር እናምናለን። ህወሓት እና አጫፋሪዎቹን ከሥልጣን ለማባረር ደግሞ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ከሕዝባዊ አመጽ ጋር ማዳቀል ስለሚኖርብን በሁሉም ረገድ ዝግጅቶቻችን አጠናቀን ለወሳኙ ፍልምያ እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! ! !**

## አዲስ አበባ ዉስጥ ወያኔ ለማፍረስ ያቀደዉን ከ5000 በላይ ቤቶችን አስመልክቶ ነዋሪዎቹ የድረሱልን ጥሪ አቀረቡ

ዘረኟዉ የወያኔ አገዛዝ በአዲስ አበባ በተለምዶ 44 ማዞሪያ ለገዳዲ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ለዘመናት ቤት ቀልሰው ኑሮቸውን እየገፉ የሚገኙ በ 10 ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በማፈናቀል ከ 5000 ሺህ በላይ ቤቶችን ለማፈራረስ ዝግጅት ማጠናቀቁን ተከትሎ የአካባቢው ነዋሪዎች ‘መሄጃ የሌለን የሃገር ውስጥ ስደተኛ ሆነናል” በማለት የድረሱልን ጥሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረባቸው ታውቋል።

በዝቅተኛ ገቢ የቀን ስራዎችን በመስራት ኑሯቸውን የሚገፉት አብዛኛዎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች ድንጋይ ፈልጠን፤ ከሠል ተሸክመን ለአንገት ማሥገቢያነት የሰራናቸውን ጎጆዎቻችን ያለምንም ተተኪ ቦታና ድጋፍ በህገወጥ መንገድ አገዛዙ በላያችን ላይ ሊያፈራርስብን ለታህሳስ 14 ቀን 2007 አ.ም ቀጠሮ ይዟል ሲሉ ብሶታቸውንና በፋሺስታዊው አገዛዝ እየደረሰባቸው ያለውን በደል ለኢትዮጵያ ህዝብ ገልጸዋል። “እኛ መሠደጃ የሌለንም፤ ኢትዮጵያዊ ሆነን እንደ ባዳ ህዝብ ተገፍተናል፤ ለጥያቄዎቻችን መልስ ተነፍገናል ኢትዮጵያዊ የሆኑ ወገኖቻችንን ሁሉ ይርዱን” ሲሉ ጥሪያቸውን ለህዝብ ያቀረቡት አባወራዎች ቤቶቻቸው ከፈረሱባቸው በኋላ መግቢያ እንደሌላቸውና ከፊት ለፊታቸው የሚጠብቃቸው የጎዳና ህይዎት እንደሆነ አስታውቀዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ከአስከፊው የጎዳና ህይወት ይታደጋቸው ዘንድ መማጸናቸውንም ለማወቅ ችለናል።

ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ለዘመናት ከሚኖሩበት ህጋዊ ቤታቸው በግፍ በማፈናቀል፤ ቤቶቻቸውን በማፈራረስ፤ ጉጅሌዎቹ መሬቶቻቸውን በሊዝ እየቸበቸቡ እንደሚገኙ እየተከታተልን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ከዚህ ህገ ወጥ ዘረፋ ጋር በተያያዘ ቀላል የማይባሉ የአገዛዙ ሙስኛ ሹማምንቶች ሐብት ማካበታቸው ይታወቃል።

## የአየር ኃይል አብራሪዎች ከነ ሂሊኮፕተራቸዉ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

አንስተው በመታገል ላይ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ሌሎችም በተለያዩ የመንግስት መስሪያቤቶች እና ተቋማት የሚሰሩ የትግራይ ተወላጆች የፋሺስታዊውን የወያኔ አገዛዝ እድሜ ለማሳጠር ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር በመሆን የበኩላቸውን የትግል አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ።

በመጨረሻም የአየር ሐይል አብራሪው ሻምበል ሳሙኤል እና ቴክኒሻኑ ጸጋብርሃን ግደይ የወሰዱት የአሁኑ እርምጃ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የአገዛዝ ዘመኔን ያራዝሙልኛል ብሎ የሚተማመንባቸው የትግራይ ተወላጆች ፋሺስታዊ አገዛዙን ጥለው መውጣታቸው እንዳስደነገጠውና የአብራሪዎቹን እርምጃ ተከትሎ ሌሎችም የሰራዊቱ አባላት አገዛዙን ከድተው ሊሄዱ ይችላሉ የሚል ስጋት ውስጥ መግባቱን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአየር ሃይል ደህንነቶች ወደ ጠፉት አብራሪዎች ቤት በድንገት በመሄድ ፍተሻዎችን ያካሄዱ ሲሆን፣ በቤቶች ውስጥ የተገኙ ሰነዶችን፣ የበረራ ማኑዋሎችን፣ የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችን፣ ትጥቆችንና ሌሎችም ቁሳቁሶች ወስደዋል።ከደህንነቶች ጋር ምንም አይነት ፖሊስ ያልነበረ ሲሆን፣ ደህንነቶች ፍተሻውን ለማካሄድም የፍርድ ቤት ማዘዣ አላሳዩም። የመከላከያ ሰራዊት ባወጣው መግለጫ ሁለቱ አብራሪዎች በዋናው አብራሪ ተገደው መጥፋታቸውን ቢገልጽም፣ ከዋና አብራሪው ውጭ ያሉት ረደት አብራሪውና ቴክኒሻኑ ቤታቸው እንዲፈተሽ መደረጉ፣ ሚኒስቴሩ የሰጠው መግለጫ የተሳሳተ መሆኑን እንደሚያመለክት ምንጮች ገልጸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚህና በመጪው ሳምንታት በድሬዳዋ ምድብ ሊደረጉ የታሰቡ የበረራ ልምምዶች ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቋረጡ ተደርጓል። ግምገማው እስኪጠናቀቅና መመሪያ እስከሚወርድ ማንኛውም የበረራ ልምምድ እንዳይደረግ የተላለፈውን ትእዛዝ ተከትሎ፣ የአየር ሃይል የደህንነት ሰዎች የተለያዩ ሰልጣኝ አብራሪዎችንና ነባሮችን እያስጠሩ በመጠየቅ መረጃ እየሰበሰቡ ነው። ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

# የባህር ዳር መስዋዕትነት የማይቀረዉ ድል ዋስትና ነዉ

ወያኔ በየአመቱ ህዳር ወር መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያን ብሄር ብረሰቦች ሰብስቦ ዘፈን የሚያስዘፍንበትን በዐል ሲያከብር በተደጋጋሚ ከሚያሳማቸዉ መፈክሮች አንዱ የብሄር ብሄረሰቦች መብትና እኩልነት በህገመንግስታችን ተከበረ የሚል እጅግ በጣም አሳሳች የሆነ መፈክር ነዉ። በእርግጥም ወያኔ ለይስሙላ ወረቀት ላይ ያሰፈረዉ ህገ መንግስት መግቢያዉ ላይ "እኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች፤ ብህረሰቦች፤ ህዝቦች በነጻ ፍላጎታችን የህግ የበላይነትና በራሳችን ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን ተነስተናል" ይላል። መቼም ይህ ምንም በማያሻማ መልኩ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ህገ መንግስታዊ አንቀጽ ሌላ ትርጉም ካልሰጡት በቀር የአማራንም ህዝብ ያጠቃልላል የሚል ሙሉ እምነት አለን። በዚህ ደግሞ የአማራን ክልል የማስተዳድረዉ እኔ ነኝ ባዩ ባዕዴንም የሚስማማ ይመስለናል። በተግባር ሲታይ ግን ይህ የወያኔ ህገ መንግስት ላይ ህዝብና መንግስት የሚተዳደሩበት ህግ ቀርቶ ህገ አራዊት እንኳን አይመስልም። ምክንያቱም በህገ አራዊት አሰራር ተመሳሳይ ዝሪያ ያላቸዉና በአ ያላቸዉ የዱር አራዊት ይከባበራሉ እንጂ አንዱ ሌላዉን አያጠፋም። ለምሳሌ አንበሳና አንበሳ ይረዳዳሉ ወይም አብረዉ አደን ይወጣሉ እንጂ እርስ በርስ አይተላለቁም፤ ነብርና አንበሳም ቢሆኑ በተገናኙ ቁጥር ተከባብረዉ ይተላለፋሉ እንጂ እንደ ወያኔ ብጤያቸዉን ባዩ ቁጥር አያጠቁም ወይም አይገድሉም።

ወረቀት ላይ የሰፈረዉን የወያኔ ህገ መንግስት የተመለከተ ሰዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎች መብታቸዉና ነጻነታቸዉ ተከብሮ የሚኖሩ ሊመስለዉ ይችላል። በእርግጥም ይመስላል። ምክንያቱም የወያኔ ህገ መንግስት ችግሩ አጻጻፉ ላይ ወይም ይዘቱ ላይ ሳይሆን በተግባር አተራጓጎሙ ላይ ነዉ። በ1987 ዓም የፀደቀዉ የወያኔ ህገ መንግስት በተግባር ሲታይ ብሄሮች፤ ብህረሰቦችና ህዝቦች የሚለዉ ቦታ ደብዛዉ ጠፍቶ ሁሉም ነገር ወያኔ ወይም ህወሓት በሚለዉ ቃል ተተክቷል፤ ወይም ሁሉም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ተጨፍለቀዉ የትግራይ ልሂቃን ወይም የህወሓት ሎሌዎችና ተላላኪዎች ሆነዋል። ለዚህ ነዉ አገራችን ኢትዮጵያ ወያኔ ያሰኘዉን የሚያዝባት የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ አንገቱን ደፍቶ የሚታዘዝባት አገር የሆነችዉ።

ሌላዉ ወያኔ ህገ መንግስቱ ዉስጥ አስፍሮ በየቀኑ እንደቤቱ ዉስጥ ምንጣፍ ከሚረግጣቸዉ ህገ መንግስታዊ አንቀጾች ዉስጥ አንዱ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ አንድ ነዉ። ይህ አንቀጽ ማንኛዉም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሠላም የመሰብሰብና ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ ሙሉ መብት አለዉ ይላል። ሆኖም የዚህን አንቀጽ ሙሉ ቃል ከወያኔ የየቀኑ አረመኔነት ጋር ስናነጻጽር አንቀጹ የተጻፈበትን ወረቀት ያክል እንኳን ክብደት የለዉም። ይህንን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ሠላማዊ ሠልፍ ባደረገባቸዉ ቦታዎች ሁሉ ወያኔ በተከታታይ በወሰዳቸዉ አረመኔያዊ እርምጃዎችና በፈጸማቸዉ ሰቆቃዎች ተመልክተናል። ለምሳሌ ባለፈዉ አመት አምቦ ዉስጥ አሁን ከሰሞኑ ደግሞ ባህርዳር ዉስጥ ህገ መንግስታዊ መብታቸዉን ተጠቅመዉ ጥያቀያቸዉን ሠላማዊ ሰልፍ በማድረግ ያቀረቡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ህፃናት፤ ወጣቶች፤ አዋቅዎች ወንዶችና ሴቶች በአግዓዚ ነብሰ ገዳዮች ጥይት ተጨፍጭፈዋል።

ወያኔ በተደጋጋሚ ሠላም ... ሠላም እያለ በአፉ ይናገር እንጂ ወያኔን ከሰላም ጋር የሚያገናኘዉም ሆነ ወያኔ ስለ ሰለም የሚያዉቀዉ ምንም ነገር የለም። እዉነቱን ለመናገር ኢትዮጵያ ዉስጥ ሠላማዊ ሠልፈኞችን የሚገድል፤ ሠላለማዊ ዜጋን አስሮ የሚደበድብና የሠላም መንገዶችን ሁሉ ቅርቅር አድረጎ የዘጋዉ ወያኔ ብቻ ነዉ። ሌላዉ ቀርቶ ወያኔ የሚያስበዉ፤ የሚያቅደዉና ዕቅዱን ወደ ተግባር የሚለዉጠዉ ከህዝብ ፈቃድና ፍላጎት ዉጭ ስለሆነ ልማት ብሎ የሚጀምራቸዉ ፕሮጀክቶች እንኳን የህዝብን ሠላም የሚያናጉና የሠላማዊ ዜጎችን ህይወት የሚቀጥፉ ጅምሮች ናቸዉ። ከሰሞኑ ደግሞ ባህር ዳር ዉስጥ እየታየ ያለዉ ህዝባዊ ቁጣ የዚሁ ወያኔ ልማት እያለ የቀሰቀሰዉ ህዝባዊ እሳት ዉጤት ነዉ።

ወያኔ እራሱን ልማታዊ መንግስት እያለ እየጠራ በሚወስዳቸዉ እርምጃዎች ሁሉ ከህዝብ ጋር መጋጨት ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። ደቡብ ኦሞ ዉስጥ ሙርሲዎች በልማት ስም ከመሬታቸዉ ተፈናቅለዋል፤ አንፈናቀለም ብለዉ የተፋጠጡት ደግሞ በግፍ ተጨፍጭፈዋል። ታሪካዊዉ ዋልድባ ገዳም ዉስጥ ገዳም አለም በቃኝ ያሉ ሰዎች መኖሪያ እንጂ የእርሻ ቦታ አይደለም ብለዉ የተናገሩ መነኮሳት ቆባቸዉን እንደደፉ በቆመጥና በሰደፍ ተደብድበዋል። ጋምቤላና አፋር ዉስጥም በልማት ስም ከመሬታችን አታፈናቅሉን ብለዉ አቤቱታ ያቀረቡ ገበሬዎች ታስረዋል፤ ተግዘዋል ተገድለዋል። ለመሆኑ ወያኔ ልማት ብሎ አንድ ፕሮጀክት በጀመረ ቁጥር ህዝብን የሚያግዝና የሚገድል ከሆነ ልማቱ የሚታቀደዉ ለማነዉ? በልማቱስ ተጠቃሚ የሚሆነዉ ማነዉ?

በያዝነዉ ታህሳስ ወር መግቢያ ላይ ባህር ዳር ዉስጥ የአራት ሰላማዊ ዜጎችን ህይወት የቀጠፈዉና አለም በቃኝ ብለዉ ለፈጣሪያቸዉ ያደሩትን መነኩሴ ጨምሮ ለአያሌ ሠላማዊ ዜጎች መቁሰልና መታሰር ምክንያት የሆነዉ ይሄዉ ወያኔ በልማት ስም የጀመረዉና የአካባቢዉን ህዝብ ፍላጎት ያላካተተዉ የወያኔ ፀረ ህዝብና ፀረ አገር እርምጃ ነዉ። በእርግጥም አሁንም ድረስ ያልበረደዉ የባህር ዳሩ ህዝባዊ ተቃዉሞ የተቀሰቀሰዉ ወያኔ የባህር ዳርና የአካባቢዉ ህብረተሰብ የጥምቀት በዐል የሚያከብርበትንና የቤ/ክርስቲያን ንብረት የሆነዉን የቅዱስ ታቦት ማደሪያ ቦታ መንገድና ሱቅ እሰራለሁ ብሎ ማፈራረስ በመጀመሩ ነዉ።

ይህ በልማት ስም ሐይማኖታዊ የማመለኪያ ቦታን የማፈራረስና የቤ/ክርስቲያንን መሬት የመቀማት ሴራ የተዉጠነጠነዉ በወያኔ ቢሆንም የወያኔ ተላላኪ በመሆን ይህንን ከፍተኛ ወንጀል በገዛ ወገኖቹና ለጥቅሙ ቆሚያለሁ በሚለዉ ህብረተሰብ ላይ የሚያስፈጸመዉ ግን ባዕዴን ነዉ። ባዕዴን ከዚህ ቀደምም በተከታታይ እንደታየዉ አማራዉ ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በግፍ ሲባረርና ሲፈናቀል አፉን ዘግቶ የተመለከተና የአማራን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለወያኔ አሳልፎ የሰጠ ከሃዲ ድርጅት ነዉ። ባዕዴን ነኝ ብሎ እንደሚናገረዉ በእርግጥም ለአማራ ህዝብ መብትና ነጻነት መከበር የቆመ ድርጅት ቢሆን ኖሮ የለየለት የአማራ ህዝብ ጠላት የሆነዉ ህወሓት ያገባዉ ገብቶ በአማራ ህዝብ ጉዳይ ላይ ሲፈተፍት ዝም ብሎ አይመለከትም ነበር።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክና አንድነት ብቻ ሳይሆን ባህሉን ፤ወጉንና ሐይማኖቱን ጭምር እንዳላነበረ ለማድረግ ያላደረጉት ነገር የለም። የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤ/ክኢርስቲያን ጳጳስ አንስተዉ ቅዱስ መንበራቸዉን እጁ በደም ለተጨማለቀ ካድሬ በመስጠት ጥንታዊት ቤ/ክርስቲያናችንን ለሁለት አንድትከፈል አድርገዋል። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሏቸዉ ከሰሞኑ ባህርዳር ዉስጥ ህዝብ ጥምቀተ በዐል የሚያከብርበትንና የቅዱስ ታቦት ማደሪያ የሆነዉን ቦታ ከቤ/ክርስቲያን ቀምተዉ የንግድ ቦታ ለማድረግ ሞክረዋል። የእስልምና እምነት ተከታዮችን በተመለከተም ህጋዊዉን መጂሊስ አፍርሰዉ በእነሱ ፍላጎት ብቻ የሚመራ አሻንጉሊት መጂሊስ በማቋቋማቸዉ ከህዝብ ሙስሊሙ ጋር የፈጠሩት ግጭት ዛሬም ድረስ እንደተቀጣጠለ ነዉ።

የወያኔ ነብሰ ገዳዮች አዲስ አበባ፤ አምቦ፤ ደቡብ ኦሞ፤ ጋምቤላ፤ አፋርና አሁን በቅርቡ ደግሞ ባ\ህርዳር ዉስጥ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የፈጸሙት አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እነዚህ ሰዎች ስራቸዉ አገር መምራት ነዉ ወይስ ህዝበን እያደኑ መግደል ነዉ የሚያሰኝ ነዉ። በእርግጥም ወያኔ እስከዛሬ የገደላቸዉን ሰዎችና ሰዎቹን የገደለበትን ምክንያት ስንመለከት የወያኔ የሙሉ ግዜ ስራ አገር መምራት ሳይሆን ህዝብን ምክንያት እየፈለገ መጨፍጨፍ መሆኑን ያረጋግጥልናል። በተለይ በቅርቡ ባህርዳር ዉስጥ አለም በቃኝ ብለዉ ገዳም የገቡትን መነኩሴ በጥይት መትተዉ ማቁሰላቸዉን ስንመለከት ወያኔዎች የገነቡትን ዘረኛ ስርዐት ዕድሜ ለማራዘም ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይሉ በግልጽ ያመለክታል።

አለማችን ዛሬም ብዙ ጨቋኝ መሪዎች የሚኖሩባት የአምባገነኖች መድረክ ናት፤ ሆኖም ህዝብ በተቃወማቸዉና በሠላማዊ ሠልፍ ቁጥዉን በገለጸ ቁጥር እንደ ወያኔ ያለ ምንም ማመንታት ህዝብን በጥይት የሚጨፈጭፍ አረመኔያዊ አገዛዝ የለም። እዚህ ላይ አንድ ፍጹም ግራ የሚያጋባ ነገር አለ፤ እሱም ወያኔ ሠላማዊ ሰለፍኞችን በጥይት የሚጨፈጭፈዉ ሆን ብሎ ህዝብን የሚያስቆጡና የሚያነሳሱ ፀር ህዝብና ፀረ አገር እርምጃዎችን እየወሰደ ነዉ። ለምሳሌ ብዙዎቹን የወያኔ ጭፍጨፋዎች ትተን ሰሞኑን ባህርዳር ላይ የደረሰዉን እልቂት ብቻ ብንመለከት ህዝባዊ ቁጣዉ የተቀሰቀሰዉ ወያኔ ካልጠፋ ቦታ የቅዱስ ታቦት ማደሪያ የሆነዉን ቦታ አፍርሶ የሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫ ቦታ ለማድረግ በመሞከሩ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሀይማኖቱ ሲነካ ወይም ሀይማኖታዊ ስርዐቱና ልምዱ ጣልቃ ሲገባባቸዉ እጅግ በጣም የሚቆጣና ተኝቶ የማያድር ህዝብ ነዉ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ህዝብ ቤ/ክርስቲያኑ አላግባብ ከፈረሰበትና ጥምቀት፤ ገና፤ ፋሲካ፤ ቡሄ፤ ቅዱስ ዮሐንስና ደመራን የመሳሰሉ ሀይማኖታዊ ስርዐቶቹንና ልምዶቹን በለመደበት ግዜና ቦታ እንዳያከብር ከተከለከለ፤ በከልካዮቹ ላይ መነሳት ብቻ ሳይሆን እነሱን ከማጥፋት የማይመለስ ህዝብ ነዉ። ዛሬ አገር ቤትም ሆነ በዉጭ አገሮች የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ አይኖቹን ወደ ባህር ዳር ያዞረዉና እኛም ዉጧ የባህርዳር ከተማ የወያኔ መጨረሻ የተጀመረባት ከተማ ናት ብለን አፋችንን ሞልተን የምንናገረዉ ይህንን ስለምንረዳ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ግፍና መከራ ከ23 አመታት በላይ ተሸክሞ ኖሯል። በእነዚህ ሃያ ሦስት አመታት ዉስጥ ሠላማዊ ኢትዮጵያዉያን በየመንገዱና በየአደባባዩ እንደ ዱር እንስሳ እየታደኑ ተገድለዋል። አዲስ አበባ፤ አምቦ፤ አዋሳ፤ደቡብ ኦሞ፤ አፋር፤ ጋምቤላ፤ አርሲ ገደብ አሳሳና ኮፈሌ ዉስጥ አሁን ከሰሞኑ ደግሞ ባህር ዳር ዉስጥ የንጹህ ኢትዮጵያዉያን ደም በግፍ እንደ ጎርፍ ሲፈስ ተመለከትናል። ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን አስወግደን ኢትዮጵያን የህዝቦቿ አገር ካላደርግናት በቀር ወያኔ ስራዉ መግደል ነዉና እሱ እየገደለ እኛም የእያንዳንዳችን ተራ እስኪደርስ ድረስ ወያኔ የገደለዉን እየቀበርን መኖራችን የማይቀር ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ያለህ አማራጭ አንድ ብቻ ነዉ፤ እሱም ሁሌ እየሞትክና እየቀበርክ ከምትኖር ከወያኔ ጋር ፉት ለፊት ተጋፍጠህ እንዳባቶችህ የክብር ሞት ሙትና ለልጆችህና ለልጅ ልጆችህ ህይወት ሁንላቸዉ። አንተ በአንድነት ተነስተህ ፊትህን ወደ ወያኔ ካዞርክ ወያኔ እንደ ጉም በንኖ የሚጠፋ ገለባ ነዉ። ወያኔ እየረገጠ የሚገዛህና የሚገድልህ አንተኑ እንደ ሀይል በመጠቀም ነዉና ለወያኔ አልገዛም በል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በዚህ በያዝነዉ የሞትና የሽረት አመት ወያኔን ለማስወገድ ከዉጭም ከዉስጥም በሚደረገዉ ትግል ዉስጥ ድርሻህን ተወጣ። ድል ምንግዜም ያንተ ነዉና . . . . አይዞህ፤ በርታ ዝመት!

## ወያኔን ከድተዉ ኤርትራ የገቡት ፓይለቶች ጉዳይ ኢትዮጵያውያንን በዓለም ዙሪያ እያነገረ ነዉ

ባሳለፍነው አርብ የአየር ሃይል ባልደረባ የሆኑት ሻምበል ሳሙኤል ግደይ፣ መቶ አለቃ ቢልልኝ ደሳለኝ የበረራ ቴክኒሻኑ ጸጋ ብርሃን ግደይ በጋራ በመሆን የሚያበሩትን የውጊያ ሄሊኮፕተር ይዘው ፋሺስታዊውን አገዛዝ በመክዳት ኤርትራ የመግባታቸው ነገር በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ መነጋገሪያ ሆኖ መቀጠሉ የሚታወቅ ሲሆን ጉዳዩን ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የተለያዩ አለማቀፍ ሚዲያዎችን ትኩረት በመሳቡ ሰፊ ሽፋን ሰጥተው እየተቀባበሉ እየዘገቡት እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

ሮይተርስ የዜና አውታር እብሪተኛው ወያኔ ስለ ሄሊኮፍተሩ ምንም አይነት ዝርዝር መረጃ አለመስጠቱን የገለጸ ሲሆን ከተለያዩ አካላት ባገኘው መረጃ መሰረት ግን ወደ ኤርትራ የገባው የጦር ሄሊኮፍተር MI 35 የተባለ ተዋጊ ሄሊኮፕተር መሆኑን መረዳት እንደቻለ ዘግቧል። የፋሽስቱ ወያኔም ሆነ የኤርትራ መንግስት በጉዳዮ ዙሪያ ዝርዝር መረጃ ከመስጠት መቆጠባቸውን ያመለከተው ሮይተርስ የጦር ተዋጊ ሄሊኮፕተሩ በሁለቱ አገራት የድንበር አዋሳኝ በኩል በመጠቀም የመኮብለል ድርጊቱን እንደፈጸመ በዘገባው አትቷል። ወርልድ ቡለቲን የተሰኘ መጽሄት በበኩሉ የዘረኛው ሕወሓት መከላከያ ሚኒስተር የፓይለቱን ኩብለላ በኤርትራ ወኪሎች በኩል የተፈጸመ መሆኑን መግለጹን ለንበባብ ባበቃው ዘገባው ገልጿል። ዴይሊ ሜል የተሰኘው የእንግሊዝ ጋዜጣ በበኩሉ የሄሊኮፕተሩን ወደ ኤርትራ መኮብለል አስመልክቶ ተመሳሳይ ዘገባ አስነብቧል። በተጨማሪም የኒዮርክ ታይምስ፤ ኤቢሲ ኒዩስ፤ ያዎ ኒውስ እና ኒውስ 14 ለጉዳዮ ሰፊ ትኩረት በመስጠት ሰፊ ዘገባ አቅርበው ለአለም ህዝብ ማስነበባቸውን ለማወቅ ችለናል።

ካለማቀፍ መገናኛ ብዙሃን ጎን ለጎን በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ዘገባዎችን የሚያዘጋጁ ድህረ ገፆች በጉዳዮ ዙሪያ ሰፊ ዘገባን ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የሚገኙት የሕወሓት ቱባ ሹማምንት በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ከመስጠት መቆጠባቸውን አመልክተዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛው የሕወሓት አገዛዝ MI 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተሩን በቅርቡ ከሩስያ በውድ ዋጋ መግዛቱ የታወቀ ሲሆን ከዘጠኝ አመት በፊት መመረት የጀመረው ይህ የጦር ሄሊኮፕተር በቀን እና በምሽት ጭምር በአየር እና በየብስ ላይ የውጊያ አገልግሎትን መስጠት የሚችል እጅግ የዘመነ ሄሊኮፕተር መሆኑን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ተናግረዋል። የጦር ሄሊኮፕተር በትንሹ እስከ 35 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሆኑን እየተሰጡ ካሉ መረጃዎች ለማወቅ ችለናል።

በተያያዘ ዜና በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የሚገኙት የዘረኛው ሕወሓት የአየር ሃይል ሹማምንቶች አስቸኳይ ግምገማ ከተጠሩ በሁዋላ እርስ በርስ እየተገማገሙና አገዛዙን ከከዱት አብራሪዎችና ቴክኒሻን ጋር ግንኙነት አላቸው ብለው የሚጠረጥሩትን የአየር ሃይል አባላት ለማሰር እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የውስጥ ምንጮቻችን አመልክተዋል። ግምገማው በከፍተኛ አለመስማማትና ትርምስ መቀጠሉን ያደረሱን ምንጮቻችን ምናልባትም ከግምገማው በኋል ሊታሰሩ የሚችሉ አባላት መኖራቸው ተመልክቷል። ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ብቻ እየደረሰባቸው በሚገኘው ዛቻና ወከባ ህይወታቸው አደጋ ውስጥ የገባ የአየር ሐይል አባላት ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አለመሆኑንም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ነፍሰ በላው አገዛዝ የግድያ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚችሉ አባል ሊኖሩ እንደሚችሉ ተነግሯል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአየሩ ገኖ ወጣ እንጂ የምድሩ ጦር በሰራዊት ውስጥ የተንሰራፋውን ዘረኝነትና ጎሰኝነት በመሸሽ በየእለቱ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የሰራዊት አባላት አገዛዙን እየከዱ እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በየ ወሩ ከ 200 በላይ የሚሆኑ የእግረኛ ሰራዊት አባላት አገዛዙን እየከዱ እርቃኑን በማስቀረት ወደ ጎረቤት አገሮች እየሸሹ እንደሚገኙ ታውቋል። አብዛኞቹ የሰራዊት አባላትም መዳረሻቸውን ኤርትራ በማድረግ በኤርትራ ውስጥ እየተደራጁ የሚገኙትን የነፃነት ሃይሎች እየተቀላቀሉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

## አለም አቀፉ ምህረት ጠያቂ ድርጅት እንግሊዝ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ባስቸኳይ ማስፈታት እንዳለባት አሳሰበ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን የጸጥታ ሃይሎች ታፍነው ለፋሺስቱ የወያኔ አገዛዝ ተላልፈው የተሰጡበትን 6 ኛ ወር አስመልክቶ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው መግለጫ በአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ ላይ እንግሊዝ ለወራት ያሳየችውን ለዘብተኛ አቋም በማብቃት ዜጋዋን ከሞትና ከስቃይ ለመታደግ እርምጃ መውሰድ እንዳለባት ድርጅቱ አበክሮ አሳስቧል። የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ ላለፉት 6 ወራቶች ያክል አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ያሉበትን ሁኔታ በይፋ አለማሳወቁ ህገ ወጥ ድርጊት መሆኑን ያስታውቀው አምንስቲ ኢንተርናሽናል እንግሊዝ እርምጃዋን ማጠናከር እንዳለባት ለአገሪቱ መንግስት ባቀረበው ደብዳቤ አመልክቷል። እንግሊዝ አቶ አንዳርጋቸው ምንም አይነት ስቃይ እንዳይደርስበትና በቤተሰቦቹ እንዲሁም በህግ ባለሞያዎች የመጎብኘት ሰብአዊ መብቱ የሚከበርበት ሁኔታ እንዲረጋገጥ ጥረቷን ማጠናከር ይኖርባታል ሲሉ የድርጅቱ የእንግሊዝ ሐላፊ ካቲ አለን ተናግረዋል።

በሰኔ ወር 2006 ከሰንአ ኤርፖርት የታፈኑት የንቅናቄያችን ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በእንግሊዝ የዲፖሎማቲክ አባላት ዘንድ የመጎብኘት እድል ተሰጥቷቸው የነበረ ቢሆንም በግል ነፃ ሆነው ከዲፕሎማቶች ጋር የመወያየት እድል ተነፍገው መገኘታቸውን የአምንስቲ ኢንተርናሽናል ባለስልጣናት አስታውቀዋል። ሰሞኑን በ 6 ስት ወራቶች ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የመጎብኘት እድል አግኝተው የነበሩት የንቅናቄያችን ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በእስር ቤት በታሳሪዎች ላይ አረመኔያዊ የማሰቃየት ተግባር በሚፈጽሙ የፋሺስታዊው አገዛዝ ሐይሎች የስቃይ ሰለባ ይሆናሉ የሚል ስጋት ከተለያዩ አካላት እየተሰነዘረ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ ዜና አንድ እንግሊዛዊ ባህር ዳር ውስጥ በእብሪተኛው ወያኔ ቅጥረኛ ሚሊሻ በጥይት ተደብድቦ መገደሉ ታውቋል። እንግሊዛዊ ጧት ላይ ባዶ እጁን ጊዮርጊስ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ሲንቀሳቀስ በሚሊሺያው በጥይት ተደብድቦ የተገደለ ሲሆን ግድያው ሲፈጸም ቅጥረኛ ፖሊሶች በቦታው መኖራቸውን ለማወቅ ችለናል።

በቅርቡ እብሪተኛው ወያኔ በ 12 ስዊድናውያን ዜጎች ላይ ሊያደርስ የነበረው የግድያ ሙከራ መክሸፉን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ይህ በሆነ በጥቂት ቀናት ልዩነት ውስጥ እንግሊዛዊው ሊገደል መቻሉ ታውቋል። ጉዳዩን በተመለከተ የእንግሊዝ መንግስት ምንም መግለጫ እስካሁን ባይሰጥም ተቀማጭነታቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉት የእንግሊዝን ዲፕሎማቶች ጨምሮ የሌሎችም አገራት ዲፕሎማቶች የደህንነት ስጋት ውስጥ መውደቃቸውን በመናገር ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

## መድረክ ከምርጫው በፊት ሜዳው መስተካከል አለበት አለ

መድረክ ባወጣው መግለጫ በሀገራችን የምርጫ ሂደት የነበሩ ጉድለቶችንና በተለይም በ2002 የሀገራችን የምርጫ ሂደት የወረደበትን አዘቅት በሚገባ በጥልቀት ገምግሞ እነዚህን ቀደም ባሉት ምርጫዎች የነበሩ ጉድለቶችን ማረምና ማስተካከል ለ2007 ምርጫ ነፃ፣ ፍትሓዊና ዴሞክራሲያዊ መሆን የምኖረውን ወሳኝ ሚና በግልጽ ቢያስቀምጥም፣ ይህንን እውነታ በአግባቡ መገንዘብ ያልቻሉና ከ1997 እና ከ2002 ምርጫዎች ደካማ ጎኖች ተገቢውን ትምህርት ለመቅሰም ያልቻሉ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመሠረታዊ የምርጫ ችግሮች ላይ የመደራደሩን ጉዳይ ወደጎን ትተው በምርጫው ለመሳተፍ ወስነናል የሚል መግለጫ አሰቀድመው መስጠታቸው ልክ ቅንጅት በ1997 ተቻኩሎ ለኢህአዴግ የለገሰውን አይነት ድጋፍና እፎይታ እየቸሩለት ይገኛሉ ብሎአል፡፡

የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ልብ ያገኘው ኢህአዴግ፣ መድረክ ያቀረበውን የድርድር ጥያቄ ወደ ጎን ትቶ በ1997 ሳይፈቱ የቀሩ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን በ2002 የጨመራቸውን እንደ 1ለ5 የጠርናፊና ተጠርናፊ የምርጫ ሠራዊት መዋቅሩን አጠናክሮና የሕዝብ የምርጫ ታዛቢ ጉዳይንም በአስቅኝ ድራማው እያጠናቀቀ ይገኛል ብሎአል፡፡መድረክ በመግለጫው ኢህአዴግ በድርጅታዊ መዋቅሩ አማካይነት በስውር በጠራቸው ጥቂት አባሎቹ አማካይነት ቀደም ብሎ የተዘጋጁ ምልምሎቹን የሕዝብ ታዛቢዎችን አስመረጥኩ እያለ ለትዝብት ያጋለጠውን ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል ሲልም አክሏል።

ኢህአዴግ በሕዝብ መብት ላይ መቀለዱን ትቶ ሕገ መንግሥቱንና ሕግን አክብሮ ምርጫን ማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ጊዜ ሳያባክንና ሳይረፍድ ከመድረክና ሌሎችም ለዚህ ዓላማ ዝግጁ ከሆኑ ፓርቲዎች ጋር በመወያየትና በመደራደር የሀገራችን የምርጫ መሠረታዊ ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች እንጠይቃለን ብሎአል።መድረክ በባሕርዳር ከተማ በሰላማዊ አግባብ ተቃውሞ ባሰሙ ዜጎች ላይ የተፈጸመው ጥቃት የአምባገነናዊ አገዛዝ ባሕሪይ ነጸብራቅ በሚል አውግዞታል።

አገዛዙ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሕይወት ማጥፋትና የአካል መጉደልን ጨምሮ የወሰደው የኃይል እርምጃ ቀደም ሲልም የሌሎች ሀይማኖቶች ተከታይ በሆኑትና በተለያዩ አከባቢዎች በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ በተደጋጋሚ ሲፈጸም የቆየ በመሆኑ የሥርዓቱን ኃላፊነት የጎደለው አምባገነናዊ ባሕሪይ ገላጭና በምንም መልኩ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተባብሮ ሊታገለው ይገባል ብሎአል።የኢህአዴግ አገዛዝ ኃላፍነቱን ወስዶ በጥቃቱ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን በአስቸኳይ ካሳ እንዲከፍልና ጥቃቱን የፈጸሙ ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብ መድረክ ጠይቋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የአየር ኃይል አብራሪዎች ከነ ሂሊኮፕተራቸዉ

... ( ከገጽ 3 የዞረ )

ታማኝ ምንጮች እንደገለጹት ከፍተኛ የበረራ ልምድ ያላቸው ሻምበል ሳሙኤል የህወሃት ባለስልጣናት በኢትዮጵያ አየር ሃይል ላይ የሚያደርሱትን ጥፋት ከሚቃወሙት የትግራይ ተወላጆች መካከል አንዱ ሲሆኑ፣ መቶ አለቃ ቢልልኝ ደግሞ በአየር ሃይል ውስጥ የተስፋፋውን ዘረኝነት ከሚኮንኑ አብራሪዎች መካከል መሆናቸው ታውቋል። ሻምበል ሳሙኤል ለ12 አመታት መቶ አለቃ ቢልልኝ ደግሞ ለ7 አመታት አየር ሃይልን አገልግለዋል።

በሌላ በኩል መንግስት አብራሪዎቹ ሄሊኮፕተሩን ኤርትራ አሳርፈውታል የሚል መግለጫ ቢሰጥም፣ የኤርትራ መንግስት እስካሁን ምንም አይነት መግለጫ አልሰጠም። ኢሳት ሄሊኮፕተሩ የት እንዳረፈ ለማወቅ ያደረገው ሙከራም እስካሁን አልተሳካለትም።ባለፉት 6 ወራት ብቻ አየር ሃይል 11 ልምድ ያካበቱ አብራሪዎችን አጥቷል። ሁሉም አብራሪዎች ከአየር ሃይል በሚጠፉበት ወቅት የሚሰጡት ምክንያት ዘረኝነት፣ የፍትህ እጦትና የአስተዳደር መበላሸት የሚል ነው።

## ሃይለማርያም ደሳለኝ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን አስጠነቀቀ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

**ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን** በሶስት ከፍሎ እንደሚያያቸው የጠቀዉ ኃይለማርያም እነሱም በአግባቡ የጨዋታ ሕጉን አውቀው ለመንቀሳቀስ የሚጥሩ መኖራቸውንና እነዚህ ተጠናክረው ቢቀጥሉ የመንግስት ፍላጎት መሆኑን፣ ሁለተኛዎቹ ወጣገባ የሚሉ መኖራቸውንና ይህን ቢያስተካክሉ ጥሩ አቋም እንደሚኖራቸው፣ ሶስተኛዎቹ የውጪ ሃይሎች የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ የሆኑ፣ የአመጽና ብጥብጥ ውይይትና ስብሰባ ሲያካሂዱ የሚከርሙና ለሀገሪቱ ፖለቲካ ፋይዳ የሌላቸው መሆቸውን አስረድቷል፡፡

ኃይለማርያም ደሳለኝ ተቃዋሚዎች በተደጋጋሚ ከገዥው ፓርቲ ጋር ለመወያየት የሚያቀርቡትን ጥያቄ በተመለከተ ተጠይቆ ሲመልስ መጀመሪያ የስነምግባር ደንቡን መፈረም እንዳለባቸውና በዚሁ መሰረት ውይይት ማድረግ እንደሚቻል ተናግሯል፡፡ ሰሞኑን በባህዳር ከተማ ከእምነት ጋር ተያይዞ በተደረገ ሰልፍ ላይ የሞቱና የቆሰሉ ሰዎች በተመለከተም ተጠይቆ ሁኔታው እንደሚጣራና በጸጥታ ሃይሎች በኩል ጥፋት ካለ እርምጃ እንደሚወሰድ ጠቁሟዋል፡፡